# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፣ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 179 ጥቅምት 9 2004 ገጽ 1


የግንቦት 7 ዛሬ ጥሪያችን አውቀውም ሆነ ሳያውቁ፣ ፈቅደውም ሆነ ተገደው የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እየረዱ ላሉ ባለሙያዎች ነው። ከመለስ ዜናዊ አገዛዝ ራሳችሁን ለማግለል የወሰናችሁ ባለሙያዎች የአገዛዙን እድሜ ለማሳጠር በሚደረገው ትግል ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ አስተዋጽዖ በማድረግ እስከዛሬ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የበደላችሁትን ህዝብ ካሱ። ባላችሁበት ቦታም ሆናችሁ ትግሉን የማገዝ እድል አላችሁ፣ ተጠቀሙበት።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የሰሜን አፍሪቃ አምባገነኖች አንድ ባንድ እየተወገዱ ነው፣ የሊቢያው ሙአመር ጋዳፊ የሞት ጽዋን ተጎነጨ

በቱኒዚያ ተቀጣጥሎ የሰሜን አፍሪቃ ሃገራት አምባገነኖችን እየጠራረገ ያለው የህዝብ አመጽ በሊቢያ ከተቀሰቀሰ ሰባት ወራት ቦኋላ ተቃዋሚዎቻቸውን አንዴ ሽብርተኞች፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ የውጪ ቅጥረኞች ከማለት አልፈው አይጦች እያሉ ሲሳደቡ የነበሩት ሙአመር ጋዳፊ ለተቃዋሚዎቻቸው በተመኙት የአይጥ ጉድጓድ ውስጥ ለ2 ወራት ያህል ከመሸጉ ቦኋላ ከትናንት ወዲያ የሚያሳፍር ሞት መሞታቸው መላውን የአለም ህዝብ እያነጋገረ መሆኑ ታወቀ።

ሙአመር ጋዳፊ በሥልጣን ላይ በቆዩባቸው የመጀመሪያዎቹ አሥር አመት የህዝብ ፍቅር የተቸራቸው መሪ የነበሩ እንደሆነ የሚናገሩት፣ ባልተገደበ የሥልጣን ዕድሜ አገሪቱን ለመምራት የተፈጠሩ ብቸኛ ሰው አድርገው እራሳቸውን ወደ መቁጠር በመሸጋገራቸው አሁን ለደረሱበት አሳፋሪ ሽንፈትና ሞት ተዳርገዋል ይላሉ።

ጋዳፊ 42 አመታት ያህል ሥልጣን ላይ ለመቆየት የተጠቀሙበት ስልት መለስ ዜናዊ በአገራችን ላይ እያደረገ እንዳለው ህዝብ እርስ በርሱ እንዳይተማመን በጎሳና በነገድ በመከፋፈል እንደሆነ ይታወቃል። በቱንዚያ የፈነዳው ህዝባዊ ተቃውሞ ወደሊቢያ በተዛመተበት ወቅት ህዝብ ያነሳውን ጥያቄ በሰላማዊ መንገድ በመመለስ ለአገራቸውና ለራሳቸው ክብር የተሻለ አስተዋጾ ማድረግ ይችሉ የነበሩት ጋዳፊ፣ ስልጣን ላይ ለረጂም ጊዜ በመቆየት በመጣ አልደፈርም ባይነት የአምባገነኖች ትዕቢት (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በአርባ ምንጭ ነዋሪዎችና በወያኔ ዘረኛ አገዛዝ መካከል የተፈጠረው ፍጥጫ አሣሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱ ተሰማ

ዘረኛውና ፋሽስቱ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በህዝባችን ላይ እያደረሰ ያለው አፈናና ጭቆና ባስመረረው የአርባምንጭና አካባቢዋ ነዋሪዎችና በአገዛዙ መካከል በተነሳው ውዝግብ እስካሁን ወደ 65 የሚጠጉ ሰዎች መታሰራቸውን የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን ኢሳት የዘገበ ሲሆን፣ አካባቢው በከፍተኛ ውጥረት ውስጥ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሎአል።

ኢሳት በአካባቢው ያሉትን ወኪሎቹን ዋቢ አድርጎ እንዳጠናቀረው መረጃ ከሆነ፣ውጥረቱ ይበልጥ እየተባባሰ የመጣው፣ ከሁለት ሳምንት በፊት በወረዳቸው፣ በዞናቸውና በቀበሌያቸው በተንሰራፋው የመልካም አስተዳደር እጦት ምክንያት፣ ለችግር መጋለጣቸውን አዲስ አበባ በመምጣት ለመገናኛ ብዙሀን ይፋ ያደረጉ የአርሶ አደሮች ተወካዮች ለእስር መዳረጋቸውን ተከትሎ ነው።

በመጀመሪያ የታሰሩት፣ አቤቱታ ለማቅረብ አዲስ አበባ የመጡት አቶ ዳሞታ ኡታ፣ አቶ ዶኮ ኮዶ፣ አቶ ዳንኤል ዳርጫ እና ሌሎች የቀበሌው ሶስት አርሶ ደሮች ሲሆኑ፣ አሁን ግን የታሳሪዎቹ ቁጥር እስከ 65 እንደሚደርስ ተነግሯል።

"አዲስ አበባ ድረስ ሄዳችሁ ለተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጉዳዩን ተናግራችኋል" በሚል ሰበብ የአካባቢው ፖሊስ አርሶ አደሮቹን ማሰሩን የጠቀሱት ምንጮች፣ እስረኞቹም፤- በላንቴ ፣ በጨንቻ እና በአርባ ምንጭ ከተማ ፖሊስ ጣቢያዎች እንደሚገኙ ገልፀዋል።

ምንጮች እንደሚሉት፣ "አለ" በተባለው ችግር ዙሪያ ማጣራት እንዲያካሂዱ ከተመረጡ የአጣሪ ቡድኑ አባላት መካከልም፣ ሁለት የቀበሌው የግብርና ባለሙያዎች ከስራ ታግደዋል። አንዳንድ የላንቴ ቀበሌ ወጣቶችም እስርን በመፍራት ወደ አርባ ምንጭ ከተማ እየሸሹ እንደሆነ ተናግረዋል።

ባለፈው ሳምንት "ስብሰባ ስላለ፣ ፖሊስ ጣቢያ ድረስ መጥታችሁ ተሰብሰቡ" የሚል ትዕዛዝ በየቀበሌው መስተዳድሮች አማካይነት ሲተላለፍ፣ ህብረተሰቡ "መሰብሰቢያ አዳራሽ እያለ ፖሊስ ጣቢያ ግቢ ውስጥ አንሰበሰብም" ማለቱን ተከትሎ በርካታ ሰዎች መታሰር እንደጀመሩ ኢሳት ዘገቦ ነበር።

በስፍራው የሚንቀሳቀሱት ወኪሎቹን ጠቅሶ ዜናውን የዘገበው ኢሳት እንዳመለከተው የወያኔ ታጣቂዎች በህብረተሰቡ ተወካዮች ላይ የወሰዱት የጅምላ እስር እርምጃ፣ በአሁኑ ጊዜ ውጥረቱንና ፍጥጫውን እጅግ እንዳባባሰውና ወያኔ እየወሰደ ባለው እርምጃ ያኮረፈው የአካባቢው ህዝብ፣"መልካም አስተዳደር አጥተናል"ለሚለው አቤቱታችን የአገዛዙ ምላሽ እስር ከሆነ፣ ከእንግዲህ የምናደርገውን እናውቃለን" ማለታቸው ተዘግቦአል።

# ግዜ

## በተለያዩ የአውሮፓና የሰሜን አሜሪካ ሃገራት ውስጥ ሆነው የፋሽስቱን የመለስ ዜናዊን አገዛዝ ዕድሜ ለማራዘም በስለላ የተሰማሩ ኢትዮጵያዊያንን እየተከታተለ የሚያጋልጥ አንድ ግብረሃይል እንቅስቃሴ መጀመሩ ታወቀ

"ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በአገራችንና በህዝባችን ላይ እያደረሰ ያለው ሰቆቃ ሰልባ ነኝ "በሚል ሽፋን የሃሰት ማስረጃ በማቅረብ በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ የፖለቲካ ጥገኝነት ካገኙ ቦኋላ መልሰው በአገር ቤት ውስጥ የሚፈጸመውን የሙስና አፈናና የሰብአዊ መብት ጥሰት ለማጋለጥ የሚንቀሳቀሱትን ኢትዮጵያዊያንን፣ በመሰለል ለአገዛዙ መረጃ የሚያቀብሉ ኢትዮጵያዊያንን ተከታትሎ የሚመዘግብና እንደአስፈላጊነቱ ለሚኖሩበት አገራት መንግሥታት የሚያጋልጥ አንድ ኮሚቴ ተቋቁሞ ከሰሞኑ እንቅስቃሴ መጀመሩን ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰ መረጃ አመለከተ።

በደረሰን መረጃ መሠረት የኮሚቴው መቋቋም አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት ፣ ከአገራችን ሁኔታ ጋር ተመሳሳይነት ባለው ሁኔታ፣ በውጪ አገር የሚኖሩ ሶሪያዊያን በበሽር አል አሳድ የሚመራው አምባገነን የአናሳ መንግሥት በአገራቸው ህዝብ ላይ የሚያደርሰውን ሰቆቃ ለማጋለጥ የሚንቀሳቀሱትን ሶሪያዊያን እየሰለለ ለአገሩ መንግሥት መረጃ የሚያቀብል አንድ ትውልደ ሶሪያ ተግባሩ በአሜሪካን አገር ተደርሶበት የወንጀል ክስ የተመሰረተበት በመሆኑ እንደሆነና፣ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በተመሳሳይ ሁኔታ ያሰማራቸው በዚህም ተግባራቸው የሚታወቁ ሰዎች በመኖራቸው እንደሆነ ለማወቅ ተችሎአል።

በዩናይትድ ስቴት የቨርጂኒያ ክፍለሃገር ነዋሪ የሆነው መሃመድ አናስ ሱኢድ በፖለቲክ ጥገኝነት ገብቶ የአሜሪካ ዜግነት ካገኘ ቦኋላ መልሶ ለሶሪያ አንባገነን መንግስት እንደሚሰልል ለኤፍ ቢ አይ መረጃ ከደረሰ ቦኋላ በተደረገበት ክትትል ቁጥጥር ሥር ውሎ ክስ እንደተመሰረተበት ይፋ ከሆነ ወዲህ ፣ መለስ ዜናዊ የስልጣን ዕድሜውን ለማራዘም ባቋቋመው የዲያስፖራ መምሪያ አማካኝነት በትናንሽ ጥቅማ ጥቅሞች በርካታ ሰላዮችን ገዝቶ ኢትዮጵያዊያኑን ለማሰለል እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ በቸልታ መታየት እንደሌለበት የብዙዎች እምነት እና መነቃቂያ ሆኖአል ተብሎአል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ፕሬዝዳንት የነበረው የወያኔ ተለጣፊ ከሥራ ታግዶ በቁም እስር ላይ እንደሚገኝ ታወቀ

በተለያዩ አንስተኛ ጥቅማጥቅሞች በመደለል በአገራቸውና በወገናቸው ላይ ታሪክ ይቅር የማይል ወንጀል በመሥራት የዘረኛውን አምባገነን ስርአት አገዛዝ እድሜ ለማራዘም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሲያደርጉ ከነበሩ በርካታ የወያኔ ሆድ አደሮች መካከል አንዱ የሆነው ያረጋል አይሸሹም ከሰሞኑ ከሥራ እንደታገደና በቁም እስር ላይ እንደሚገኝ ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰ መረጃ አጋለጠ።

ያረጋል አይሸሹም ቀደም ሲል የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ፕሬዚዳንት ሆኖ ሲያገለግል ከቆየ ቦኋላ በፖለቲካ ታማኝነት ለወያኔው ቁንጮ መለስ ዜናዊ የሚሰጠው አገልግሎት እያነሰ በመምጣቱ ከክልል ፕሬዝዳንትነት ተነስቶ በአሁኑ ወቅት የተወካዮች ምክር ቤት አባልና የንብረት ሥራ ማኀበራት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ሆኖ እያገለገለ እንደሆነ ቢታወቅም በወያኔ ፓርላማ አባልነቱ ፣ የነበረው ያለመከሰስ መብቱን ጭምር እንደተገፈፈ የደረሰን መረጃ አክሎ ገልጾአል።

እንደ ምንጮቻችን ዘገባ መሰሪው የወያኔ አገዛዝ በያረጋል አይሸሹም ላይ ፊቱን ያዞረበት የሕግ፣ የፍትሕና የአስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በመባል በሚታወቀው የወያኔ ቡድን በሙስና ወንጀል እንደተጠረጠረ ከተገለጸለትና ያለመከሰስ መብቱ እንዲነሳ የቀረበለትን ጥያቄ መቀበሉን ይፋ ካደረገ ቦኋላ መሆኑ ታውቆአል።

ያረጋል አይሸሹም አሁን ለተዘፈቀበት ቅሌት የተጋለጠው የክልሉ ፕሬዚዳንት በነበረበት ወቅት በክልሉ እንዲሠራ በጀት ከተያዘላቸው የሦስት ትምህርት ቤቶች ማሰሪያ ገንዘብ ላይ ከክልሉ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ጋር በመመሳጠር ከ83 ሚሊዮን ብር በላይ ለግል ጥቅሙ ማዋሉ በማስረጃ በመረጋገጡና በቂ አመላካች ነገሮች በመኖራቸው ነው ተብሎአል።

በአሁኑ ጊዜ በቁም እስር ላይ የሚገኘው ያረጋል አይሸሹም የየዘውን የመንግስት ንብረት ካስረከበ በሁዋላ ወደ እስር ቤት እንደሚወርድም ተያይዞ የደረሰን መረጃ ያመለክታል።

ግለሰቦች የወያኔን አጀንዳ ሙሉ በሙሉ እስካስፈጸሙና ስብዕናቸውን በቁሳዊ ችሮታ ለውጠው ታዛዥነታቸውንና ታማኝነታቸውን እስካረጋገጡ ድረስ ለተዘፈቁበት ሙስና ተጠያቂ እንደማይሆኑ በተረጋገጠበት የመለስ ዜናዊ አስተዳደር፣ የያረጋል አይሸሹምን በሙስና ወንጀል ከሥራ መታገድና ለክስ መቅረብ ፖለቲካዊ ይዘት ያለው ነው በማለት ለግለሰቡ (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## ጥሪ በመለስ ዜናዊ ጎራ ለተሰለፉ ባለሙያዎች

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ለባለሙያዎች ከፍተኛ ክብር አለው። ሆኖም ግንቦት 7 ነፃነት በሌለበት ሃገር ውስጥ ሙያም ሆነ ባለሙያ ክብር የማይሰጣቸው፤ በክፍያም ሆነ በማስገደድ የአምባገነኑ ፈቃድ ፈፃሚዎች እንደሚሆኑ ይገነዘባል። ነፃነት በሌለበት ሃገር ባለሙያዎች ተገደው አሊያም ለመኖር በሚል ሰበብ ገንዘብ ለሚከፍል የጊዜው አምባገነን ሥርዓት በሎሌለነት ያድራሉ። ግንቦት 7 እንዲህ ያለው ሁኔታ በሀገር ላይ የሚያደርሰውን ከፍተኛ ጉዳት ስለሚረዳ፣ ባለሙያዎች ከተጽዕኖ ነፃ በሆነ መንገድ የሙያ ግዴታቸውን እንዲወጡ ሁኔታዎች ሊመቻቹላቸው ይገባል ብሎ በጽኑ የሚያምን ድርጅት ነው። የሚታገለውም ለሙያ ነፃነት መረጋገጥ ጭምርም ነው።

ሙያን ከአፋኝ የፓርቲ ፓለቲካ ተጽእኖ ነፃ ማድረግ ተገቢ የመሆኑን ያህል የሙያን ክብር አዋርዶ ለገንዘብ ብቻ ሲባል በገለልተኝነት ሽፋን ከአፋኝ ሥርዓትጋር መተባበርን ግን አጥብቀን ልንታገለው የሚገባን ጉዳይ ነው። የባለሙያዎች ግዴለሽነት የመለስ ዜናዊ አገዛዝን እስካሁን ካቆሙት ነገሮች አንዱ ነው። ለፍትህና ነፃነት ግዴለሽ የሆኑ ባለሙያዎች መኖራቸው የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ባለሙያዎቹ የቆሙለትን ሙያ ሳይቀር ለማዋረድ የሚያስችል አቅም ሰጥቶታል።

ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል:-

- ብዙ ድሆች ከእለት ጉርሳቸው ቀንሰው ያጠራቀሙት ገንዘብ ጥቂት የገዥው ቡድን አባላት በብድር መልክ እየወሰዱ በአንድ ምሽት ሲከብሩበት እያየ፤ ይህ ደግሞ ኢፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል መሆኑ እያወቀ፤ "እኔን የሚያገባኝ የሂሳብ ሚዛኑ ትክክለኝነት ነው" የሚል የባንክ ባለሙያ ከዘራፊዎች ጋር አልተባበረምን? ህሊናውንስ ሊቆጨው አይገባምን? በዚህ ተግባሩስ የሚወደውን የባንክ ሙያን አላረከሰምን?
- የገበየውን የኮምፒዩተርና፣ የኢሌክትሮኒክስም ሆነ የሶፍት ዌር ኢንጂነሪንግ እውቀት ለሬድዮ፣ ስልክና የኤሌክትሮኒክስ መልዕክቶች ጠለፋ የሚያውል ባለሙያ ሙያውን እያራከሰ አይደለምን? በተለይም ደግሞ በሙያው ለዘረኛ አምባገነን ደህንነት ሲባል የህዝብ መብት መጣሱ "ሙያተኝነቱ በቀረብኝ" አያስብልምን?
- የድሃ ገበሬዎችን ማሳ ነፃ በሚባል ዋጋ ተረክቦ ለባዕድ ባለሀብቶች አትርፎ በመሸጥ ላይ ላለው ካራቶሪ ተቀጥሮ የሚሠራ የግብርናም ይሁን የውሃ ልማት ባለሙያ ከእርሻው የተፈናቀለውን ድሃ ገበሬ እሮሮ እየሰማ "ይህ ከሙያዬ ውጭ ያለ ጉዳይ ነው፤ አያገባኝም" ቢል ሙያውን አላረከሰምን? እሱ ራሱ በግል ከዘመናዊ ጉልተኞች ጋር ተባብሯል ማለት አይቻልምን?
- ዩኒቨርስቲዎችና ኮሌጆች እንዲህ የአፈና ተቋማት ሲሆኑ፤ የትምህርት መርሃ ግብር ሲጣስ፤ ተማሪዎች በአካዳሚ እውቀት ፋንታ የውሸት ፕሮፖጋንዳ ሲሞሉ እያየ "ይኸ እኔን አያገባኝም" የሚል መምህር በትምህርት ሥርዓቱ መዋረድና መውደቅ ድርሻ የለውምን?
- ዘረኝነት፣ ወገንተኝነት፣ ሙሰኝነት ከተፃፉት ፓሊሲዎች በላይ ሥራ ላይ የዋሉ ፓሊሲዎች መሆናቸውን እያየና እያወቀ "እኔ የመንግሥት ሠራተኛ ነኝ፤ ገለልተኛ ነኝ" የሚል ባለሙያ ራሱን እያታለለ አይደለምን?
- እነዚህ ሁሉ በሙያ ሰበብ የሚታለፉ ከሆነ ማዕከላዊ እስር ቤት በዱላ የሰውን አካል እየቦጫጨቁ የሚጥሉት ገራፊዎች "መግረፍ ሙያችን ነው" ቢሉ ተቀባይነት ሊኖራቸው አይደለምን?

ፓለቲካ ለመንግሥት ሥልጣን የሚደረግ ትግል እንደሆነ ብቻ አድርጎ መውሰድ ለብዙዎች ቅን አሳቢ ባለሙያዎች "እኔ የመንግሥትን ሥልጣን አልፈልግም፤ ፓለቲካን አልወድም፤ ሥራዬን ልሥራበት" እንዲሉ መንገድ ከፍቶላቸዋል።

ሃቁ ፓለቲካ ለመንግሥት ሥልጣን የሚደረግ ትግል ብቻ አለመሆኑ ነው። ፓለቲካ ለፍትህ፣ ለሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ ለእኩልነት፣ ለክብር የሚደረግ ትግልም ጭምር ነው። ለሙያ ነፃነትና ክብር የሚደረገውም ትግል ፓለቲካ ነው። በእኛ ሀገር እውነታ ደግሞ ፓለቲካ እንደ ሰው ለመታየትና እንደ ሰው ለመቆጠር የሚደረግ ትግል ነው። በባለሙያነት ወይም በገለልተኝነት ሰበብ ከፓለቲካ መራቅ ከኃላፊነት ብቻ ሳይሆን ከገዛ ራስ ህሊና መራቅ ጭምር ነው። እራስን ማታለል ካልሆነ በስተቀር ዘረኝነትና አፈና ባለበት ሥርዓት ውስጥ አንገት ደፍቶም ቢሆን የሙያ ግዴታን መወጣት አይቻልም።

ስለሆነም የዛሬ ጥሪያችን አውቀውም ሆነ ሳያውቁ፤ ፈቅደውም ሆነ ተገደው የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እየረዱ ላሉ ባለሙያዎች ነው።

ባለሙያነታችሁን እናከብራለን። ሙያችሁ የመከራችን ማሳጠሪያ እንዲሆን እንፈልጋለን።

ይህን በማድረግ ፋንታ ግን ሙያችሁ የዘረኛ አምባገነን እድሜ እና የመከራችን ማርዘሚያ ሆኖ መገኘቱ በቸልታ የምናልፈው ጉዳይ አይደለም። የቁርጥ ውሳኔ ቀን መጥቷል፤ ዛሬውኑ መስመራችሁን አስተካክሉ። ነገ ሊረፍድ ይችላል። በሀገራችሁ፤ በወንድሞቻችሁና በእህቶቻችሁ ላይ ብዙ ውድመት ከደረሰና ብዙ ጥፋት ከተሰራ በኋላ ባለሙያነታችሁ ከተጠያቂነት አያድናችሁም።

ከመለስ ዜናዊ አገዛዝ ራሳችሁን ለማግለል የወሰናችሁ ባለሙያዎች የአገዛዙን እድሜ ለማሳጠር በሚደረገው ትግል ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ አስተዋጽዖ በማድረግ እስከዛሬ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የበደላችሁትን ህዝብ ካሱ። ባላችሁበት ቦታም ሆናችሁ ትግሉን የማገዝ እድል አላችሁ፤ ተጠቀሙበት።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

• • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • •

## በርካታ የሰራዊቱ አባላት የዘረኛና አፋኙን አገዛዝ በመቃወም የትግራይ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄን (ትህዴን) መቀላቀላቸው ተዘገበ

ባለፈው አንድ ሳምንት ብቻ በተለያዩ ቦታዎች ተመድበው የነበሩ 14 ወጣት የኢትዮጲያ ሠራዊት አባላት የዘረኛና አፋኙን የመለስ አገዛዝ በመቃወም ከትግራይ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ ጋር መቀላቀላቸውን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ዘገበ።

እንደ ኢሳት ዘገባ በምህፃረ-ቃል "ትህዴን" በመባል የሚታወቀው የትግራይ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ የወጣቶቹንና የወታደሮች ፎቶ አያይዞ ለኢሳት መግለጫ መላኩ የታወቀ ሲሆን በመግለጫው፤ የዘረኛው መለስን ሥርዓት ከድተው ወደ ትህዴን የተቀላቀሉት ወጣቶች፤ ከአማራ፣ ከኦሮሚያ፣ከትግራይና ከደቡብ ክልሎች የመጡ መሆናቸው ታውቁአል።

የፋሽስቱን አገዛዝ የከዱ የሰራዊቱ አባላት ስም ዝርዝርም፤ 1ኛ/ ወ/ር ብዙዓለም ሽፋራው እርቄ፣ 2ኛ/ አስር አለቃ ሁሴን መሃመድ አህመድ፣ 3ኛ/ ምክትል አስር አለቃ ቦጋለ ኩራቻ፣ 4ኛ/ ወታደር እድሪስ ሁሴን መሃመድ፣ 5ኛ/ አስር አለቃ ሁሴን ደመቀ ተገኘ፣ 6ኛ/ ምክትል አስር አለቃ ኢብራሂም ደግፌ ባንቲ፣ 7ኛ/ ወታደር ጸጉ ሃፍቶም መረሳ፣ 8ኛ/ አስር አለቃ ዋርሳው ባንቲ በሪሳ፣ 9ኛ/ ምክትል አስር አለቃ ታደመ ወይዳይ ጃጓድ፣ 10ኛ/ ወታደር አታኽልቲ ታረቀ ፍቃዱ፣ 11ኛ/ ፍስሃ ጸጋይ አውዓላ፣ 12ኛ/ ተወልደ መለስ መድሃንየ፣ 13ኛ/ አጸደ ማዓሾ ገ/ጻዲቕ፣ እና 14ኛ/ ምሩፅ ዕቑባሚካኤል ገብሩ መሆናቸውን ተያይዞ የወጣው ዘገባ ያመለከተ ሲሆን ወታደሮቹ የነበሩበት እዝ፣ ክ/ጦር፣ ሬጅመንት፣ ሻምበልና፣ የመቶኛ ጓዳቸው በድርጅቱ መግለጫ ላይ በዝርዝር መመልከቱን ኢሳት ዘግቡአል።

ወጣቶቹ "ትህዴን"ን ለመቀላቀል የወሰኑት፤በስልጣን ላይ ያለው የኢህአዴግ መንግስት የህዝብን ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የማያከብር በመሆኑ ምክንያት እንደሆነ የተናገሩ መሆኑ የታወቀ ሲሆን "ፀረ-ህዝቡ ስርዓት በብሄር ብሄረሰቦች ላይ እየፈጸመው ያለው በደልና ግፍ ከመቸውም ግዜ በላይ እየከፋ ነው"ያሉት ምክትል አስር አለቃ ሀሰን ደመቀና ምክትል አስር አለቃ ታደመ ወይዳይ፤ በተለይ ባለፈው ወር በሀዲያ በተነሳው ግጭት ብዙ ሰዎች መገደላቸውና በርካታዎች ያለበደላቸው መታሰራቸው እንዳሳዘናቸው መግለጻቸውን ኢሳት ዘግቡአል።

"የሰራዊቱ ከፍተኛ አዛዦች ሰራዊቱን በብሄር፣ በማእረግና በጥቅማጥቅም በመለያየት የስልጣን እድሜያቸውን እያራዘሙ ናቸው"ያለው አስር አለቃ ሁሴን መሀመድ አህመድ በተለይም ከ1997 ምርጫ በሁዋላ የተቀጠሩ አዲስ ምልምሎችን በማይጨበጥ ተስፋና በጥቅማጥቅም ለማታለል ጥረት ቢያደርጉም፤ አብዛኛው ሠራዊት በሥርዓቱ ላይ እምነት እንዳጡ መረጃዎችን በመጥቀስ መናገሩ ተዘግቡአል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የወጡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ትህዴን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረ በመምጣቱ ለገዢው ፓርቲ ከፍተኛ ስጋት በሚሆንበት ደረጃ ላይ መድረሱ ታውቁአል።

## የሰሜን አፍሪቃ አምባገነኖች አንድ ባንድ እየተወገዱ ነው፤ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ሲወጠሩና በባዶ ሜዳ ሲደነፉ ከሰነበቱ ቦኋላ ከተደበቁበት የቆሻሻ መተላለፊያ ቱቦ ውስጥ በውርደት ተጎትተው በመውጣት እንደተገደሉና ጦሱ ከራሳቸው አልፎ ለልጅ ልጆቻቸውም መትረፉ ብዙዎቹን ያነጋገረ ሆኖአል።

የጋዳፊ መገደል ዜና የተሰማው የሽግግሩ አስተዳደር ተዋጊዎች ሐሙስ እለት ማለዳ ሲርቲ ላይ አዲሱን የሊቢያ ሰንደቅ ዓላማ ከሰቀሉ በኋላ ነው። ከተማይቱን ለበርካታ ሣምንታት ሲያናጋት በከረመው የደፈጣ ተኩስና የከበድ መሣሪያ ድምፅ ቦታ ወደሰማይ በሚንጣጣ የደስታ መግለጫ ተኩስና የመኪና ክላክስ ተተክቷል። የሊቢያ የሽግግር መንግሥት ባለልስጣናት ጋዳፊ ሲርቲ ላይ በተካሄደ ውጊያ መገደላቸውን እንዳስታወቁ ጋዳፊ ለአርባ ዓመታት በገዛት ሀገርና ሌሎች ከተሞችም ፈንጠዚያ ሆኗል። ጋዳፊ ለሁለት ወራት ተሸሽጎ ሲሳደድ የቆየበት ወቅት መደምደሙ ለብሔራዊ የሽግግር መንግሥቱ በሀገሪቱ ላይ ቁጥጥሩን የሚያጠናክርበት ምዕራፍ ከፍቶለታል።

የሙአመር ጋዳፊን ሞት ተከትሎ የዝግጂት ክፍላችን ከተለያዩ ቦታዎች በኢሜይልና ስልክ መለክቶች የደረሱን ሲሆን ከአዲስ አበባ በኢሜይል ከተቀበልናቸው መለክቶች መካከል አንደኛው፣ እንዳሉት፣ የጋዳፊ ሞት ለሊቢያዊያን ርካታ ያስገኘላቸው ሲሆን የሊቢያዊያኑ ርካታ ደግሞ ለኛ ለኢትዮጵያዊያን ይተስፋ ሰጪ ሆኖልናል ብለዋል:: ቀጥለውም፣ በፍጹም ይደፈራል ተብሎ የማይታለመው የሊቢያው አምባገነናዊ አገዛዝ እንዲህ ሲገረሰስ ማየታችን መለስናና የሱን አሽቃባጮች ከሃገራችን ምድር ጠራርገን ለማጥፋት ምንም እንደማይከብደን ነው በማለት አስተያየታቸውን አጠቃለዋል።

## ሰቆቃን ለማስቀም በጋራ እንነሳ!!!

### የግንቦት 7 ርዕሰ አንቀጽ በቁጥር 134 አቅርቦት የነበረው ብሄራዊ ጥሪ

ከወያኔ እስር ቤቶች የሚደርሱን መረጃዎች ህሊናን የሚረብሹ ናቸው። የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ አባላት በእስር ላይ በሚገኙ ወገኖቻችን ላይ የሚፈጽሙት ሰቆቃ (ቶርቸር) በአስከፊ ሁኔታ ጨምሯል።

በጭካኔው "ተወዳዳሪ የለውም" ሲባል በነበረው የደርግ ዘመን እንኳን የማይታወቁ የሰቆቃ ዓይነቶች ዛሬ በንፁሃን ዜጎች ላይ እየተፈጸሙ ነው። ለማስረጃ ያህል:-

- ወንዶች የዘር ፍሬዎቻቸውን በመዶሻ ይቀጠቀጣሉ፣
- ሴቶች ጡቶቻቸውን ይረገጣሉ፣ ክብረ-ነክ ተግባራትም ይፈጸምባቸዋል፣
- በኤሌክትሪክ በሚሰራ ማሞቂያ የእስረኞችን ጭንቅላት በማጋል እንዲሰቃዩ ይደረጋል፣
- ከወንበር ጋር አቆራኝቶ ለሳምንት ያህል ማሰር በጣም እየተዘወተረ ያለ የሰቆቃ ዓይነት ሆኗል፣
- በጠባብ ክፍል ውስጥ ለብቻ ዘግቶ ለወራት ማቆየት የተለመደ ነገር ነው፣
- ከቆዳ በተሰራ ጅራፍ መግረፍ ድሮም ያለ ቢሆንም አሁን ተጠናክሮ ቀጥሏል፣ በደርግ ጊዜ የነበሩ ገራፊዎች ከያሉበት እየተፈለጉ እንደገና ለገረፋ ተቀጥረዋል፣
- በሰብዓዊ ፍጡር ላይ ካራቴና ጁዶ መለማመድ፣ በስለት መቆራረጥ ወጣት የወያኔ "ተተኪዎች" የሚወዱት መዝናኛ ሆኗል፣

እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ አሰቃቂ የሰቆቃ ዓይነቶች የወያኔ እስር ቤቶች መለያ ባህሪያት ናቸው።

የትግራዩ ገዥ ጉጅሌ ሰላዮች ሰቆቃን የሚፈጽሙ ስለመሆኑ በገሃድ አምነው አያውቁም። ሆኖም ግን ሰቆቃን የሚፈጽሙት ተከልለውና ተደብቀው አይደለም። ስንቱ ነው ከተማ ውስጥ በሰው መሃል የተደበደበው? ስንቱ ነው በአደባባይ የተረገጠውና የተዋረደው? በጠራራ ፀሃይ፣ ከተማ ውስጥ፣ ህዝብ መሃል ይህንን የመሰለ ሰቆቃ የፈጸመን እስር ቤት ውስጥ ከዚህ አንድ ሺህ ጊዜ የከፋ ነገር ከመፈጸም ምን ያግደዋል?

በማናቸውም ምክንያት ሰቆቃ መፈጸም እጅግ የተወገዘ እና ምህረት የማያሰጥ ዓለም ዓቀፍ ወንጀል ነው። የደህንነት ስጋትም ሆነ አደጋ ለሰቆቃ በምክንያትነት ሊቀርብ አይችልም። ሰቆቃን ተቀባይነት ያለው የምርመራ ዘዴ የሚያደርግ የወንጀል ዓይነት የለም። "ወንጀል መከላከል" ለሰቆቃ ተቀባይነት የሌለው ምክንያታቸው ቢሆንም እንኳ ወያኔዎች እሱንም በምክንያትነት ማቅረብ አይችሉም። የወያኔ ሰላዮችና ፓሊሶች ሰቆቃን የሚፈጽሙት የሚመረምሩት ብርቱ ወንጀል ስላለ አይደለም። ወያኔዎች በወያኔ ዳኞች ጉዳያቸው ያለቀላቸውና ወያኔያዊ ፍርደገምድል ፍርድ የተሰጣቸው ፍርደኞችንም ጭምር ያሰቃያሉ። ለወያኔ የሰቆቃ እውነተኛ ምክንያቶች ሁለት ናቸው።

የመጀመሪያዉና እና ዋነኛው ምክንያታቸው የዘር ጥላቻ ነው። የወያኔ አረመኔዎች የአማራና የኦሮሞ ተወላጆች የሆኑ ግለሰቦችን በደበደቡና ባዋረዱ መጠን አማራንና ኦሮሞን ያዋረዱ ይመስላቸዋል። ለዘመናት በልባቸው ውስጥ የተጠራቀመውን ጥላቻ በግለሰቦች ላይ ይወጡታል። እነዚህ በከፋት የተሞሉ ሰዎች ሲገርፉና ሲደበድቡ የሚሳደቡት፣ የሚራገሙት የተደብዳቢውን ዘር እንጂ ተደብዳቢውን በግል አለመሆኑ የደረሰበት ሁሉ ያውቀዋል።

ሁለተኛው ምክንያት የጉጅሌው አባላትና ተባባሪዎች ሰውን በማሰቃየት የሚደሰቱ እኩያን መሆናቸው ነው። ይህ የስነልቡና ህመም ምንጩ በራስ የመተማመን እጦት ነው። መንፈሰ ደካማ ሰው ውስጡ እየነገረው ያለውን ደካማነት በእጁ በሚሰነዝረው ዱላ ማስተባበል ይፈልጋል። የትግራይ ገዢ ጉጅሌ እና ተባባሪዎቹ የሚያደርጉት ይህንኑ ነው። እጃቸው ውስጥ የገቡትን ወገኖቻችንን በማሰቃየት ትንሽነታቸውን ማሸነፍ ይፈልጋሉ።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በወገኖቻችን ላይ ዘግናኝ ሰቆቃዎችን በማድረስ ላይ ለምትገኙ የትግራይ ገዥ ጉጅሌ አባላት፣ ለቅጥረኞቻቸውና ተባባሪዎቻቸው በሙሉ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል። ሰቆቃ ፈጽሞ ማምለጥ እንደማይቻል በደርግ ጊዜ የሰቆቃ ቀንደኛ መሪ ከነበረውና በአሜሪካ አገር ተከሶ ዛሬ በናንተው እስር ቤት ከሚገኘው ቀልቤሳ ነጌዎ ትምህርት ውሰዱ። የእናንተም መጨረሻ ከእነሱ የባሰ እንጂ የተሻለ እንደማይሆን ተገንዘቡ።

ግንቦት 7 በሰቆቃ ላይ መረጃ ማሰባሰብ የጀመረ በመሆኑ ያላችሁን መረጃዎች

በኢሜል pr@ginbot7.org እና በፖስታ
P.O.Box: 56281, London N4 9BH, United Kingdom
P.O.Box: 4916, 2003EX, Haarlem, The Netherlands
8647 Richmond Highway, 652, Alexandria, VA 22309, USA

እንድትልኩ ያሳስባል።

በመጨረሻም ሰቆቃን ከኢትዮጵያ ምድር ለማጥፋት የሚቻለው ወያኔን ማስወገድና በምትኩ ለሰው ልጅ ክብር ያለው በህዝብ የተመረጠ መንግሥት ሥልጣን ሲይዝ በመሆኑ ለዚህ ግብ ሁላችንም በአንድነት እንነሳ ይላል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## ወያኔ የራስ ዳሽን ተራራ የሚገኝበትን የሰሜን ጎንደር ወረዳ በትግራይ ክልል ሥር ለማስገባት እያደረገ ያለውን ሙከራ የበየዳ ነዋሪዎች መቃወማቸው ተዘገበ

በተፈጥሩአዊ መስህብነቱ በአለማችን የሚታወቀው የራሽ ደጀን ተራራ በሚገኝበት በዬዳ ወረዳ አካባቢ የሚኖሩ የሷሬ ቀበሌ ነዋሪዎችን፣ በትግራይ ክልል ውስጥ እንዲካተቱ ለማሳመን ለ7 ተከታታይ ቀናት የተደረገው ውይይት ሳይሳካ መቅረቱን ስማቸው እንዳይገለጥ የፈለጉ የአካባቢው ነዋሪዎች መግለጻቸውን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ዘገበ።

እንደ ኢሳት ዘገባ የትግራይ ክልል ባለስልጣናት የቀበሌው ነዋሪዎች ወደ ትግራይ ክልል እንዲዛወሩ ተደጋጋሚ ሙከራ ቢያደርጉም፣ ህዝቡ ግን እኛ በታሪክ ተወቃሽ አንሆንም፣ አያት ቅድመ አያቶቻችን አጥንታቸው የተቀበረው በዚሁ ቦታ ነው። ግዛቱ የማን እንደሆነ ይታወቃል። በማለት ጥያቄውን ውድቅ ማድረጋቸው ታውቋል።

ከዚህ ቀደም ራስ ዳሽን ተራራ በትግራይ ክልል ይገኛል በማለት በመጽሀፍ መልክ ታትሞ መቅረቡን እንዲሁም ላለፉት ተከታታይ አመታት የራስ ዳሽን አካባቢን ህዝብ ወደ ትግራይ ክልል ለማስገባት ተደጋጋሚ ሙከራ መደረጉን ያስታወሱት የአካባቢው ነዋሪዎች፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የሚታየው ግፊት ከዚህ በፊት ከታየውም የባሰ ነው ማለታቸው ተያይዞ የደረሰው ዘገባ አመልክቷል።

ትግራይ አካባቢውን ለመውሰድ ለምን እንደፈለገ የተጠየቁት ነዋሪዎቹ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአካባቢው ለቁርቁሮና ለተለያዩ እቃዎች መስሪያ የሚሆን ከፍተኛ ማእድን በመገኘቱ ሊሆን ይችላል፣ ሲሉ ግምታቸውን ማስፈራቸውንም ኢሳት አክሎ ዘግቧል።

የአካባቢው ወጣቶች የትግራይ ክልል እየፈጸመ ያለውን ተግባር በእጅጉ እየተቃወሙት ነው ያለው ኢሳት የበየዳ ወረዳ አካባቢ ህዝብ ሙሉ በሙሉ አማርኛ ተናጋሪና በታሪክም የጎንደር ግዛት መሆኑን ነዋሪዎች እንደሚናገሩ ገልጿል።

እስካሁን አካባቢውን በጉልበት ለመከለል ጥረት አለመደረጉን የሚናገሩት ነዋሪዎች፣ አሁን የሚታየው ሁኔታ ከቀጠለ በአካባቢው ግጭት ሊነሳ እንደሚችል ያስጠነቀቁ ሲሆን፣ ራስ ዳሽን ተራራ በትግራይ ክልል ይገኛል ተብሎ በእንግሊዝኛ መጽሀፍ ውስጥ መስፈሩን በማስመልከት የክልሉ መንግስት በስህተት የተፈጸመ ነው ቢልም፣ እስካሁን የማስተካከል ሙከራ አለመደረጉን ታዛቢዎች እንደሚናገሩ ታውቋል።

የበየዳ ወራደ ቀድሞ በደባርቅ አውራጃ ውስጥ ይገኝ እንደነበር የሚታወቅ ሲሆን አንዳንድ ወገኖች ራስ ዳሽን ተራራም ሆነ በዙሪያው ያለው መሬትም ሆነ ማእድን የኢትዮጵያ ህዝብ ሃብት ሆኖ እያለ፣ አላስፈላጊ የሆነ የባለቤትነት ጥያቄ በማንሳት ህዝቡ እንዲከፋፈል በማድረግ ላይ ያለው ዘረኛውና ከፋፋዩ አገዛዝ ነው ይላሉ።

## የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ፕሬዝዳንት የነበረው የወያኔ ተለጣፊ ከሥራ ታገዶ በቁም እስር . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ቅርበት ያላቸው ምንጮች ይናገራሉ። ለዚህም የሚሰጡት ምክንያት ግለሰቡ የክልሉ ፕሬዚዳንት በነበረበት ወቅት፣ ህወሀት በክልላቸው የሚያደርገውን ጣልቃ ገብነት አጥብቆ በመቃወሙ፣ በአነ አባይ ጸሀዬ የተመራ ቡድን ማስጠንቀቂያ ሰጥቶት እንደነበርና ማስጠንቀቂያውን ተከትሎም በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የሚገኙ ተቃዋሚዎችን ትደግፋለህ የሚል ክስ ቀርቦበት ከፕሬዚዳንትነት እንዲነሳ እንደተደረገ ይገልጻሉ።

ያረጋል አይሸሹም ከወያኔ አመራር ጋር እልህ እንደተጋባ "ለደህንነቴ እሰጋለሁ" በማለት በህክምና ሰበብ ወደ ኬንያ ከተጓዘ ቡኋላ በዩጋንዳ በኩል ወደ ካናዳ በመሄድ ጥገኝነት ለመጠየቅ ሙከራ አድርጎ እንደነበርና የጥገኝነት ማመልከቻውን ይከታተሉለት ለነበሩት ሳያማክር ብድግ ብሎ ወደ አገር ቤት እንደተመለሰና መልሶ ለዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ማገንበሱን እንደቀጠለ መዘገቡ ይታወሳል።

ከምርጫ 97 ቡኋላ ወያኔን እየተዉ የሚኮበልሉ ባለስልጣናት ቁጥር በመጨመሩ ስጋት የገባው የመለስ አገዛዝ፣ የያረጋል መኮብለል ለሌሎች አረአያነት እንዳይኖረው ፈርቶ የሆዱን በሆዱ በመያዝ ጊዜያዊ ምህረት እንዳደረገለትና ከነበርበት የክልል ፕሬዝዳንትነት አንስቶት በቅርብ ርቀት ሊቆጣጠረው ወደሚችልበት አዲስ አበባ በማምጣት በፌደራል መንግስቱ መስሪያቤት እንደመደበው ይታወቃል። በወያኔ ጣልቃ ገብነት ተማሮና ለህይወቱ ሰግቶ ከአገር ወጥቶ የነበረው ያረጋል አይሸሹም በወቅቱ በቅርበት ይገናኙት ለነበሩ ሰዎች "አገር ቤት ጥሎአቸው በመጣ ቤተሰቦቼ በማሳበብ "የስደትን ህይወት ሊለምደው እንደማይችል ገልጾ እንደተመለሰ ምንጮች ይናገራሉ።

ወያኔ ሥልጣን ላይ ለመደላደል እንደመሳሪያ የተጠቀመባቸውን የሌላ ብሄረሰብ አባላትን እንደአገዳ ከመጠጣቸው ቡኋላ አንድ በአንድ ጎዳና ላይ አውጥቶ እንደምጥላቸው ይታወቃል።

## ስር እየሰደደ በመሄድ ላይ ስላለዉ የኢትዮጵያ የሰብኣዊ መብት ረገጣ የተነጋገረ ሕዝባዊ ስብሰባ በለንደን ተካሄደ

የፋሽስቱ መለስ ዜናዊ አገዛዝ ከጊዜ ወደ ጊዜ በህዝብ ላይ እየፈጸመ ስላለው የሰብኣዊ መብት ረገጣ በሰፊው የተነጋገረ አንድ ታላቅ ህዝባዊ ስብሰባ ከትናንትና ወዲያ እሁድ (16/10/2011) በእንግሊዝ አገር በሎንደ ከተማ በፍሬንድ ሃዉስ አዳራሽ ውስጥ መካሄዱን ከስፍራው የደረሰን ዜና አመለከተ።

ቁጥራቸው ወደ ሁለት መቶዎች የሚገመቱ ኢትዮጵያዊያን በተገኙበት በተካሄደው በዚህ ታላቅ ስብሰባ ላይ ተገኝተው የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የ3ኛዉ አለም የሁሉም የፓርላማ ቡድኖች ህብረት ሊቀመንበር የሆኑት የተከበሩ ካዉንስለር ሙሽራክ ላሺር መሆናቸው ተያይዞ የደረሰን ዘገባ አመለከተ። ካዉንስለሩ በመክፈቻ ንግግራቸዉ በኢትዮጵያ ዉስጥ ያለዉ የሰብኣዊ መብት አያያዝ እጅግ አሳሳቢ እንደሆነ በመግለፅ ከዚህ በፊት በተመሳሳይ ምክንያት የሶስተኛዉ አለም ህብረት የፓርላማ ቡድን ከኢትዮጵያ የዲሞክራሲና የሰብኣዊ መብት ተሟጋቾች ጋር በመተባበር ሁለት የህዝብ ስብሰባዎች ማካሄዱን ገልጸው ፤ በኢትዮጵያ ዉስጥ ገንዘብና ስልጣን ከፍተኛ የሆነ ሙስናን ብሎም የሰብኣዊ መብት ረገጣን ሊያስከትሉ እንደቻለ አስረድተዋል።

“ሕዝብ በረሃብና በድህነት በሚሰቃይባት አገር ጠ/ሚኒስትሩና ደጋፊዎቹ በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ በዉጭ አገር በማካበት ላይ ናቸው ያሉት ካውንስለር ሙሽራክ፤ የምእራቡም አለም "በፀረ ሽብር ተባባሪነት" ስም በህዝብ ላይ የሚደርሰዉን የመብት ጥሰት ችላ ብለውታል፤ ስለዚህ ኢትዮጵያዊያን ህብረት ፈጥረዉ በጋራ መንቀሳቀሳና በለንደን በሚገኙት በፓርላማ ተወካዮቻቸዉ አማካይነት በህዝብ ላይ የሚደርሰዉን ግፍና ስቃይ የብሪታኒያ መንግስት ይበልጥ እንዲረዳዉ ማድረግ እንደሚኖርባቸው በማሳሰብ በመጪዉ ነሃሴ ወር በእንግሊዝ ፓርላማ ውስጥ በኢትዮጵያ ስለሚካሄደው ምርጫ ውይይት እንደሚካሄድ ጠቁመዋል።

ማስ አድቮኬሲ ፎር ሂዩማን ራይት ኢን ኢትዮጵያ፤ የተባለዉ ቡድን ባዘጋጀዉ በዚህ አራት ሰዓታት በፈጀ ስብሰባ ላይ ንግግር ያደረጉት ሌላው ተጋባዥ እንግዳ በቅርቡ ኢንቬስቲጌቲቭ ጆርናሊዝም ቢሮ ከቢቢሲ ኒዉስ ናይት ጋር በመተባበር በኢትዮጵያ ለድሃዉ ህብረተሰብ የሚሰጠዉ የዉጭ ርዳታ የገዢዉ ፓርቲ/ህወሃት/ የፖለቲካ መጨቆኛ መሳሪያ መሆኑን ያጋለጡት ጋዜጠኛ አንገስ ስቲክለር ነበሩ።

ጋዜጠኛ አንገስት ስቲክለር ባደረጉት ንግግር እሳቸዉና ባልደረቦቻቸዉ ያጠናቀሩትን መረጃ የኢትዮጵያው አገዛዝ አምኖ አለመቀበሉ የሚጠብቁት ነገር እንደነበረ ገልጸው ፤ በየገጠሩ ተዘዋዉረዉ ያገኙት ማስረጃ በእጃቸዉ እንዳለና በሰሩት ስራ ሙሉ እምነት እንዳላቸዉ ጠቅሰው ፤ በተዘዋወሩባቸዉ መንደሮችና ሰፈሮች ዉስጥ መረጃ የሰጧቸዉን ድሃ ገበሬዎች የመለስ መንግስት የፀጥታ ሃይሎችን በማሰማራት፤ በማሰስና በማፈላለግ በንፁሃን ዜጎቹ ላይ ያደረሰባቸዉ ወከባና እንግልት እጅግ አሳዛኝ እንደሆነ ገልጸዋል።

የመለስ አገዛዝ በኦጋዴን ሶማሌ ክልል በህዝብ ላይ የሚፈፅመዉን የሰብኣዊ መብት ጥሰት ለመከታተል በሚስጢር የገቡትን ሁለት የስዊድን ጋዜጠኞችና ሌሎችም ኢትዮጵያዊያን ጋዜጠኞችና የተቃዋሚ ድርጅት መሪዎችን በሽብርተኝነት እንዳሰራቸዉና ክስ እንደመሰረተባቸዉ አንገስ አስታዉሰዉ፣ በህግ ወንጀለኛነታቸዉ ሳይረጋገጥ ጠ/ሚር መለስ ሽብርተኞች ናቸዉ በማለት ፍርድ መስጠቱን በአገሪቱ ውስጥ እየተካሄደ ያለውን የፍትህ አሰራር ምንነት ያሳያል ብለዋል።

የኢንቬስቲጌቲቭ ጆርናሊዝም ቢሮ፤ የብሪታኒያ መንግስት የሚሰጠዉ የርዳታ ገንዘብ ለተረጂዎች ላለመድረሱ አሳማኝ ማስረጃ እያለ የአለም አቀፍ የዉጭ ርዳታ የካቢኔ ሚኒስትር አንድሪዉ ሚቼል ስለጉዳዩ ለማስተባበል ያደረጉት ጥረት ወይ ባለማወቅ ወይ ሆን ተብሎ የተፈፀመ ክህደት መሆኑን የጠቀሱት ጋዜጠኛ አንገስት፣ ግብር ከፋዩ የብሪታኒያ ህዝብ እዉነቱን ማወቅ መብቱ እንደሆነ በማመን ድርጅታቸዉ የሚኒስትሩን ማስተባበያ በቀላሉ እንደማይመለከተዉና ሌሎች ተጨማሪ ጥያቄዎች መነሳታቸዉን አስረድተዋል።

በማያያዝም በአገሪቱ በመካሄድ ላይ ያለዉ የሰብኣዊ መብት ረገጣ በገለልተኛ አካል እንዲጣራ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ልዩ ራፖርተር ጥያቄ መቅረቡንና ራፖርተሩም እንዲጣራ አምኖ ጥያቄዉን መቀበሉን አስረድተዋል።

ጋዜጠኛ አንገስት ስቲክለር፤ መለስና እርሱ የሚመራው ፓርቲ በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ብሪታኒያን ጨምሮ ከምእራቡ አለም በገፍ እየተቀበሉ የኢህአዴግ ደጋፊ ያልሆኑትን ለማጥቃትና በረሃብ ለመቅጣት በፖለቲካ መሳሪያነት እየተጠቀሙበት እንዳለ ያጋለጡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለዉለታ በመሆናቸዉ ተሰብሳቢዉ ለጋዜጠኛ ስቲክለር ያለዉን አድናቆት በከፍተኛ ጭብጨባ እንደገለጸላቸው ታውቆአል።

የኢንቬስቲጌቲቭ ጆርናሊዝም ቢሮ በኢትዮጵያ ዉስጥ በድብቅ በመዘዋወር ከድሃዉ ገበሬና ህብረተሰብ ጋር በመነጋገር አገሪቱ ከዉጭ የምታገኘዉ ርዳታ የገዢዉን ፓርቲ /ህወሃት/ ለሚደግፉ ብቻ እንደሚዉል ያጋለጡበት የ22 ሰዓት የቪዲዮ ፊልም ቀረፃ በእጃቸዉ እንዳለና ከዚህ ዉስጥ የተጠቀሙት የ17 ደቂቃ ብቻ እንደሆነ ጋዜጠኛ አንገስ ለኢሳት በሰጡት አጭር ኢንቴርቪው መግለጣቸውን ኢሳት በትናንትናው እለት ዜናው ዘግቦአል።

## መለስ ዜናዊና ግብረአበሮቹ “በህዳሴው ዋዜማ ላይ እንገኛለን” በማለት በሚቀልዱበት በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ በዳቦ እጥረት እየታመሰች መሆኗ ተዘገበ

ወያኔ መላውን አገራችንን በመሳሪያ ሃይል በመቆጣጠር ከዛሬ 20 ዓመት በፊት ስልጣን ሲቆጣጠር የኢትዮጵያን ህዝብ በመጀመሪያው 10 አመት ቢያንስ በቀን ሶስት ጊዜ እንዲበላ እናደርገዋለን በማለት የሃሰት ተስፋ የሰጠ ሲሆን መለስ ዜናዊና ጥቂት ግብረአበሮቹ በተከተሉት የአገር ሃብት ምዝበራና ዘረፋ ምክንያት ከ20 ዓመታት የወያኔ የስልጣን ዘመናት ቦኋላ ዛሬ አገራችን ታይቶ በማይታወቅበት የድህነት አረንቋ ውስጥ እንደገባችና በቀን አንድ ጊዜ እንኳ ለመመገብ የማይችለው የህብረተሰባችን ቁጥር ከቀን ወደ ቀን እጅግ እየጨመረ መምጣቱ ታወቀ።

ቀደም ሲል በድህነት ወለል ላይ ነው ይባል የነበረው የህብረተሰብ ክፍል ሳይቀር በቀላሉ ያገኝ የነበረው ዘይትና ሳሙና ዛሬ እንደ ቅንጦት ዕቃ እየተቆጠረ እንደሆነ የሚናገረው የአገራችን ህዝብ በተለይ ካለፉት ሁለት ወራት ወዲህ ደግሞ በዳቦ እጥረት ጭምር እየታመሰ እንደሚገኝ ከአዲስ አበባ የሚወጡት ዜናዎች ያመለክታሉ።

የችግሩን መንሰኤ በግልጽ ለመናገር ወያኔ የሚያደርሰው የፖለቲካ ጥቃት ስጋት የፈጠረባቸው የአዲስ አበባ አስተዳደር ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ችግሩ የተከሰተው በስንዴ ዱቄት አለመኖር ነው ሲል የቆየ ቢሆንም የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት የተባለው በመጋዘን ውስጥ በቂ ክምችት አለ በማለት ለማስተባበል መሞከሩ ብዙዎችን እያስገረመ ነው።

አድስ አበባ ውስጥ ያለውን የዋጋ ንረት የሚከታተሉ ዘጋቢዎቻችን የስንዴ ዋጋ ካለፈው ሚያዚያ ወር ጀምሮ እጅግ እየናረ መምጣቱን የገለጹ ሲሆን የህዝብን ብሶት ለማቀዝቀዝ ሲባል ወያኔ በመጋዘን አለኝ ሲል የነበረውን ክምች ላለፉት አምስት ወራት በንግድ ሚኒስቴር አማካይነት ለየ ዳቦ ቤቶች በረሽን መልክ ሲያከፋፈል እንደቆየ ይናገራሉ። ሆኖም የነበረው ክምችት እየተሟጠጠ በመምጣቱ ከመስከረም ወር ጀምሮ ዳቦ ቤቶች በከፍተኛ ደረጃ የዱቄት እጥረት አጋጥሟቸዋል ተብሎአል።

የዱቄት እጥረቱን ተከትሎ በርካታ ዳቦ ቤቶች የዳቦ ግራምን እስከመቀነስ እንደደረሱ የዘገበው ዘጋቢያችን የዳቦዎች መጠን ያለመጠን ማነስ እያነጋገረ ባለበት ሰዓት ይባስ ብሎ በመዲናይቱ ከሚገኙ ዱቄት ፋብሪካዎችና ዳቦ ቤቶች መካከል አብዛኞቹ ስራቸውን እንዳቆሙ ገልጾአል። የሸዋ ዳቦና ዱቄት ፋብሪካ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ፀሀዬ ዘሙ፤ በዱቄት እጥረት ምክንያት በአዲስ አበባ ውስጥ ካሏቸው 65 ዳቦ ቤቶች 45 ቱን መዝጋታቸውን እንዳስታወቁና በተጨማሪ በቀን እስከ 350 ቶን ዳቦ የመጋገር አቅም ያለውን የዳቦ ማምረቻ ኢንደስትሪያቸውን መዝጋታቸው ተያይዞ የደረሰን ዜና ያስረዳል።

## በተለያዩ የአውሮፓና የሰሜን አሜሪካ ሃገራት ውስጥ ሆነው የፋሽስቱን የመለስ ዜናዊን አገዛዝ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ኢትዮ ሚዲያ በመባል የሚታወቀው ድረገጽ ባለፈው ሳምንት እንደዘገበው ከአውሮፓ የኮበለሉ ከፍተኛ የኤምባሲ መልእክተኞች በተለይ በቤልጂየም እና በሆላንድ ነዋሪ ኢትዮጵያውያንን እየሰለሉ መረጃ የሚያስተላለፉ ሰላዮች ስም ዝርዝር ለዝግጅት ክፍሉ መላካቸውን ገልጾአል። ድረ ገጹ በበኩሉ አክሎ እንደገለጸው የእነዚህን ሰላዮች ስም ዝርዝር ከህግ ባለሞያዎች ጋር ተማክሮ ይፋ እንደሚያደርግና፣ እነኝህ የወያኔ ሰላዮች በከፊል ለዚሁ እኩይ ተግባር በወያኔ በስደተኝነት ስም ወደ አውሮፓ የተላኩ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ በአዲስ አበባ የመኖርያ ቤትና ቦታ ለማግኘት ሲሉ በረሃብ እያአለቀ ባለው ወገናቸው ላይ ይቅር የማያሰኝ ደባ እየፈጸሙ ያሉ መሆናቸውን ገልጹአል።

በርካታ መረጃዎች እንደሚያረጋግጡት የዘረኛው መለስ አገዛዝ በአሜሪካ፣ በአውሮፓ፤ በአውስትራሊያ እና በአፍሪካ ሀገሮችም ሳይቀር በሚሊዮን ዶላር በጀት በመመደብ ከረጂም አመታት በፊት ጀምሮ ሰላዮቹን እንዳስማራ ከኮበለሉ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ሰራተኞች እንዲሁም በውጪ ሃገራት ለኤምባሲዎች በማገልገል ላይ ከሚገኙና ቅርበት ካላቸው ምንጮቻችን ያገኘነው መረጃ ይጠቁማል።

አሜሪካዊ ዜግነት ያለው የ47 አመቱ ሶርያዊ መሃመድ አናስ ሱኢድ በውጭ የሚኖሩ ሶርያውያንን የፖለቲካ እንቅስቃሴና የተቃውሞ ሰልፎችን በስእል እና በድምጽ በመቅረጽ፤ በስደት የሚኖሩትን በማስፈራራት እና በልዩ ልዩ ዘዴዎች በማወክ፤ ተግባር ላይ ተሰማርቶ የነበረ በመሆኑና መረጃዎችንም ለባሻር አል አሳድ መንግስት በማቀበል ሲሰራ እንደነበር የተደረሰበት በስደት የሚኖሩ የሶርያ ተወላጆች ባደረጉት ክትትል እና ጥቆማ መሆኑ ታውቆአል።

ኢትዮጵያዊያን ስደተኞች በመካከላቸው ሆነው የወንጀለኛውን መለስ ዜናዊ አገዛዝ ዕድሜ ለማራዘም ሌት ተቀን የስለላ ሥራ የሚሰሩትንና መረጃ በማቀበል የሚታወቁትን ሰላዮች በተደገፈ ማስረጃ በማጋለጥ እንዲተባበሩ አስተባባሪ ኮሚቴው ጥሪውን እያቀረበ በዝግጅት ክፍላችን

**የስልክ አድራሻ** 0044203 286 9661 **ወይም**
0044 208 133 5670 **እንዲሁም**
**በኢመል አድራሻችን** g7radio@ginbot7.org **ወይም**
PR@ginbot7.org

ብትልኩልን ጥቆማችሁን ለኮሚቴው የምናደርስ መሆናችንን በአክብሮት እንገልጻለን።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz
እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:00 እስከ 2:30 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን። ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org